የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ተልቢያቸው "ለበይከ አልላሁምመ ለበይክ፣ ለበይከ ላ ሸሪከ ለከ ለበይክ፣ ኢነልሐምደ ወንኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላ ሸሪከ ለክ" (አላህ ሆይ! ደግሜ ደጋግሜ ለጥሪህ አቤት እላለሁ፤ ምንም ተጋሪ የለህም። ምስጋና ፀጋና ንግስና ለአንተ ብቻ ነው፤ ምንም ተጋሪ የለህም።) የሚል ነበር።

ከዐብደላህ ቢን ዑመር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ተልቢያቸው "ለበይከ አልላሁምመ ለበይክ፣ ለበይከ ላ ሸሪከ ለከ ለበይክ፣ ኢነልሐምደ ወንኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላ ሸሪከ ለክ" (አላህ ሆይ! ደግሜ ደጋግሜ ለጥሪህ አቤት እላለሁ፤ ምንም ተጋሪ የለህም። ምስጋና ፀጋና ንግስና ለአንተ ብቻ ነው፤ ምንም ተጋሪ የለህም።) የሚል ነበር። ዐብደላህ ቢን ዑመር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እዚህ ላይ "ለበይከ
ለበይከ ወሰዕደይክ፣ ወልኸይሩ ቢየደይክ፣ ለበይከ ወርረግባኡ ኢለይከ ወልዐመል" (ጥሪህን ተቀብያለሁ፣ ለጥሪህ ምላሽ እሰጣለሁ፣ መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ ነው፤ ምኞትና ተግባር ወደ አንተ ይመራል።) የሚለውን ይጨምሩ ነበር።» [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ወደ ሐጅ ወይም ዑምራ ተግባር መግባት ሲፈልጉ ይሉት የነበረው ተልቢያ እንዲህ ብለው ነበር: (ለበይከ አልላሁመ ለበይክ) አላህ ሆይ! ወደ ጠራኸን ተውሒድ፣ ስራን ለአላህ ማጥራት፣ ለሐጅና ለሌሎችም አምልኮዎች ቁርጠኛ የሆነ መቀበልን ደጋግሜ ተቀብያለሁ። (ለበይከ ላ ሸሪከ ለከ ለበይክ) አንተ ብቻ ነህ አምልኮ የሚገባህ፣ በጌትነትህ፣ በተመላኪነትህና በስሞችህና በባህሪያቶችህም አጋር የለህም። (ኢነል ሐምደ) ምስጋናና ውዳሴ ላንተ ነው የሚገባህ። (ወንኒዕመተ) ፀጋም (ለከ) ከአንተ ነው። አንተው ነህ የምትሰጠን። በሁሉም ሁኔታዎች የምታስተናብረው አንተ ነህ። (ወልሙልኩ) ንግስናም ያንተ ነው። (ላሸሪከ ለክ) የሚጋራህ የሌለ ሁሉም ያንተ ብቻ ነው። ኢብኑ ዑመር - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እዚህ ተልቢያ ላይ ይህን ይጨምሩ ነበር፡ (ለበይከ ለበይከ ወሰዕደይክ) ደጋግሜ ጥሪህን እቀበላለሁ፤ አስደስተኝ። (ወልኸይሩ ቢየደይክ) ሁሉም መልካም የሚገኘው በችሮታህ ነው። (ለበይከ ወርረግባኡ ኢለይክ) ልመናና ፍላጎታችንም የምንፈልገው መልካም ነገርም በእጅህ ወደሆንከው ወዳንተ ነው። (ወልዐመሉ) ስራም ለአንተ ነው። አምልኮ የሚገባው ለአንተ ብቻ ነው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/4535